# 2024 ቦንድ ሪፈረንዳ

## 1. የባቡር መጓጓዣና ትራንስፖርት

**ጥያቄ: የአርሊንግተን ካውንቲ እዳ ተዋውሎ አጠቃላይ የግዴታ ማስያዣዎችን በከፍተኛው የእዳ መጠንን $72,405,000 ዶላር ፋይናንስ ለማድረግ፣ ከሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች ጋር ለዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ትራንዚት ባለስልጣን (WMATA) እና ሌሎች የመጓጓዣ፣ የእግረኛ፣ የመንገድ ወይም የትራንስፖርት ፕሮጀክቶችን ይፈቅዳል?**

ማብራሪያ:

ይህ ምክረ ሃሳብ በካውንቲው ውስጥ ለተለያዩ የመጓጓዣ፣ የመንገድ፣ የእግረኞች ማሻሻያና የመጓጓዣ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ምክረ ሃሳብ መሰረት ሊደገፉ የሚችሉ የፕሮጀክቶች የሚጠበቁ ወጪዎች $44.3 ሚሊዮን ዶላር የአርሊንግተን ካውንቲ የWMATA/የሜትሮ ካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም ድርሻ በከፊል ለመደገፍ፣ $22.0 ሚሊዮን ዶላር የአካባቢ መንገዶችንና የመኪና መንገዶችን አስፓልት ለማልበስ የተወሰነውን ወጪ ለመሸፈን፣ $1.5 ሚሊዮን ዶላር የእግረኛ መንገድን፣ የመንገድ ጠርዝንና የጎርፍ መገደቢያ ዞን ለመጠገን፣ $1.3 ሚሊዮን ዶላር ለመንገድ ሙብራትና ለሌሎች የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፎች ናቸው፡፡ የካውንቲው ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተሻሻለው በካውንቲው የካፒታል ማሻሻያ እቅድ ውስጥ ካሉ ሌሎች የመጓጓዣ ፕሮጀክቶች መካከል የካውንቲው ቦርድ አስፈላጊ በሆነው ወይም በሚፈለገው መጠን የቦንድ ገንዘቦች ላይ እንደገና ድልድል ሊያደርግ ይችላል፡፡

**<u>2024 ቦንድ ሪፈረንዳ</u>**

**2. <u>የአካባቢ ፓርኮች እና መዝናኛዎች</u>**

**<u>ጥያቄ:</u> የአርሊንግተን ካውንቲ እዳ ተዋውሎ አጠቃላይ የግዴታ ማስያዣዎችን በከፍተኛው የእዳ መጠንን $25,770,000 ዶላር ፋይናንስ ለማድረግ፣ ከሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች ጋር ለአካባቢያዊ ፓርኮችና መዝናኛዎች የተለያዩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ወጪዎችን ይፈቅዳል?**

<u>ማብራሪያ:</u>

ይህ ምክረ ሃሳብ ለተለያዩ ፓርኮችና መዝናኛ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክረ ሃሳብ መሰረት ሊደገፉ የሚችሉ የፕሮጀክቶች የሚጠበቁ ወጪዎች ለሶስት የከተማ ፓርኮች $8.1 ሚሊዮን ዶላር፣ ለፓርኮች ጥገና ካፒታልና ማስተር ፕላን ፕሮጀክቶች $5.8 ሚሊዮን ዶላር፣ ለእረኛ መንገድና ድልድይ ማዘመኛ $3.4 ሚሊዮን ዶላር፣ $2.4 ሚሊዮን ዶላር ለኬንሞር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአትሌቲክስ ሜዳ ማሻሻያና ለሌሎች ፓርኮችና መዝናኛ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ የካውንቲው ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተሻሻለው በካውንቲው የካፒታል ማሻሻያ እቅድ ውስጥ ካሉ ሌሎች ፓርኮችና መዝናኛ ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ በሆነው ወይም በሚፈለገው መጠን የቦንድ ገንዘቦች ላይ እንደገና ድልድል ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 2024 ቦንድ ሪፈረንዳ

**3. የማህበረሰብ መሰረተ ልማት**

**ጥያቄ፡ የአርሊንግተን ካውንቲ እዳ ተዋውሎ አጠቃላይ የግዴታ ማስያዣዎችን በከፍተኛው የእዳ መጠንን $76,150,000 ዶላር ፋይናንስ ለማድረግ፣ ከሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች ጋር ለመገልገያ ካፒታል፣ ለተቋማት ንድፍና ግንባታ፣ የአርሊንግተን አካባቢ ፕሮግራምና ሌሎች የካውንቲ መሰረተ ልማትን ጨምሮ ነገር ግን በነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ የካፒታል ፕሮጄክቶች ወጪዎችን ይፈቅዳል?**

ማብራሪያ፡

ይህ ምክረ ሃሳብ ለተለያዩ የካውንቲ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክረ ሃሳብ መሰረት ሊደገፉ የሚችሉ የፕሮጀክቶች የሚጠበቁ ወጪዎች $14.0 ሚሊዮን ዶላር ለአርሊንግተን አካባቢ ፕሮግራም፣ $13.8 ሚሊዮን ዶላር ለተቋማት የጥገና ፕሮግራም፣ $9.2 ሚሊዮን ዶላር ለፍርድ ቤት/ለፖሊስ ሕንጻ ማሻሻያ፣ $8.1 ሚሊዮን ዶላር ለካርሊን ስፕሪንግስ ቦታ፣ $6.0 ሚሊዮን ዶላር ለኩዊንሲ ቦታ፣ $6.0 ሚሊዮን ዶላር ለቢሮ ቦታ መገልገያና ለሲስተም እቃዎች ፣ $4.9 ሚሊዮን ዶላር ለሁኔታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ማእከል እንዲሁም የህዝብ ደህንነት፣ ኮሙዩኒኬሽንና የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር መምሪያና ለሌሎች የካውንቲ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ የካውንቲው ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተሻሻለው በካውንቲው የካፒታል ማሻሻያ እቅድ ውስጥ ከሌሎች የካውንቲና የማህበረሰብ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ በሆነው ወይም በሚፈለገው መጠን የቦንድ ገንዘቦች ላይ እንደገና ድልድል ሊያደርግ ይችላል፡፡

**4.** ***መግለጊያዎች***

***ጥያቄ፡*** **አርሊንግተን ካውንቲ እዳ ተዋውሎ አጠቃላይ የግዴታ ማስያዣዎችን በከፍተኛው የእዳ መጠንን $14,220,000 ዶላር ፋይናንስ ለማድረግ፣ ከሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች ጋር ለአርሊንግተን ካውንቲ የውሃ ብክለት መቆጣጠሪያ ፋብሪካና ለካውንቲው አገልግሎት የሚሰጡ የውሃና የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችን የመንደፍ፣ የማስፋት፣ የማሻሻል እና የማደስ ወጪዎችን ይፈቅዳል?**

***ማብራሪያ፡***

ይህ ምክረ ሃሳብ ለካውንቲው የፍሳሽ ማስወገጃ፣ ውሃና የፍሳሽ መሰረተ ልማት ጉልህ ማሻሻያዎችን ይደግፋል፡፡ በቦንድ ፈንድ ሊደገፉ የሚችሉ የፕሮጀክቶቹ የሚጠበቁ ወጪዎች $9.4 ሚሊዮን ዶላር ለዋሽንግተን የውሃ ማስተላለፊያ ስርዓት ካፒታል ማሻሻያ፣ $2.5 ሚሊዮን ዶላር ለውሃ-ዋና መተኪያ ፕሮግራም፣ $1.3 ሚሊዮን ዶላር ለዝቃጭ ፍሳሽ ማስወገጃ #1 (ASE1) የመምጠጫ ጣቢያ ፕሮጀክት፣ $0.5 ሚሊዮን ዶላር ለንግድ ማእከል መሳሪያዎችና ማሻሻያዎች እንዲሁም $0.5 ሚሊዮን ዶላር ለተጠናቀቀ የውሃ ማስተማመኛና ትስስር ናቸው፡፡ የካውንቲው ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተሻሻለው በካውንቲው የካፒታል ማሻሻያ እቅድ ውስጥ ካሉ ሌሎች የፍጆታ ፕሮጀክቶች መካከል የካውንቲው ቦርድ አስፈላጊ በሆነው ወይም በሚፈለገው መጠን የቦንድ ገንዘቦች ላይ እንደገና ድልድል ሊያካሂድ ይችላል፡፡

**<u>2024 ቦንድ ሪፈረንዳ</u>**

**1. <u>የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች</u>**

**<u>ጥያቄ፡</u> የአርሊንግተን ካውንቲ እዳ ተዋውሎ አጠቃላይ የግዴታ ማስያዣዎችን በከፍተኛው የእዳ መጠንን $83,990,000 ዶላር ፋይናንስ ለማድረግ፣ ከሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች ጋር ለአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ካፒታል ፕሮጀክቶችን ይፈቅዳል?**

**<u>ማብራሪያ፡</u>**

ይህ ምክረ ሀሳብ ለአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም ገንዘብ ያስገኛል፡፡ በዚህ ምክረ ሀሳብ መሰረት ሽፋን የሚያገኙ የፕሮጀክቶች የሚጠበቁ ወጪዎች፡

- ዋና የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ($24,600,000 ዶላር)
- የኬንሞር ሰራሽ በሳር የተሸፈነ ሜዳ ($2,440,000 ዶላር)
- የሃውስ ሞንቴሶሪ አርሊንግተን ህዝብ ትምህርት ቤትን ወደ የሙያ ትሩፋት ሕንጻ ማእከል ማደስ ($45,470,000 ዶላር)
- የማብሰያ ቤትና የመግቢያ እድሳት (11,480,000 ዶላር ዶላር)

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተሻሻለው በየትምህርት ቤቱ የካፒታል ማሻሻያ እቅድ ውስጥ ካሉት የትምህርት ቤት ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ በሆነው ወይም በሚፈለገው መጠን የቦንድ ገንዘቦች ላይ እንደገና ድልድል ሊያደርግ ይችላል፡፡